# ሃያ አምስት የባከኑ አመታት!

**ገ/ፃዲቅ አበራ**

ግንቦት 20/ 2008

ግንቦት 20 ሲታሰብ ስለ ሕወሓት/ኢህአዴግ ገዳይነትም ሆነ አፋኝነት የማይጠራጠሩና የሚታየውን እውነታ የሚቀበሉ ወገኖች ጭምር፣ ሃገሪቱን በከፍተኛ ደረጃ ስላሳደገ የሚል ማካካሻ አስተያየት ሲሰጡ ይደመጣሉ። የሞባይል ቴሌፎን፣ ኢንተርኔት ያገኘነውና ዘመኑን የተጠጋነው በእነርሱ ነው ብለው የሚያሞግሱ፣ "በዕድገት ግስጋሴ ላይ ነን.." የሚለውን ተቀብለው ይህንኑ የሚያስተጋቡና ስረዓቱን የሚያንቆለጳጵሱ የዋሆችም፣ እንዲሁም እውነቱ ያልጠፋቸው አድርባዮችም ባጃቢነት ቀጥለዋል።

የስርዓቱ ሰዎችና ዓለምን በጠባቧ ሰማይ - በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በኩል የሚመለከቱ የዋሆች፣ እንዲሁም ሆዳቸው ህሊናቸው ላይ የበረታ ደካሞች ያሉት ሁሉ እውነት ቢሆንና ኢትዮጵያ በእርግጥም በዕድገት እየገሰገሰች ቢሆን እንኳን፣ ነጻነት በቁስ የማይለወጥ በመሆኑ፣ በባርነት ውስጥ ጮማ ከመቁረጥ፣ በነጻነት ጥሬ እየቆረጠሙ መኖር ጤና እና የህሊና ሰላምን ይሰጣል።

የኢትዮጵያችን ሁኔታ የሚያሳዝነው ግን በባርነትም ውስጥ ቢሆን ለምርጫ የቀረበው ፣ ጮማ እየቆረጡ ባርነትን መቀበል ሳይሆን፣ ጮማ የሚቆርጡትን እያዩ ፣ የእነርሱን ሕንፃ እያደነቁ ተስፋ እንኳን በሌለበት ነገን ጭምር እየፈሩ መኖር ነው። ሁሉ ነገር ይቅርና ሲበሉም እያየን፣ ሕንፃቸውንም እያደነቅን እንደነርሱ ባይመቸን እንኳን፣ በእርግጥ በቀን ሦስት ጊዜ መብላት የምንችልበትን፣ በልቶ ማደር ቅንጦት ሆኖ መቀጠሉ የሚያበቃበትን መንገድስ ጀምረናልን?! በርግጥስ በሕወሃት/ኢሕአዴግ አመራር ተስፋ ይታያልን?! በሕወሃት የሚመራው የኢሕአዴግ መንግስት ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት እንደዋንኛ ስኬቱ የሚቆጥረውና አንዳንዶች በመረጃ ዕጦት፣ ሌሎች በአደርባይነት፣ የቀሩትም በድንቁርና የሚናገሩለት የኢኮኖሚ ዕድገት፣ በተለይ ሳትዛነፍ የቀጠለችው አስራ-አንድ በመቶ (11%)፣ በገለልተኛ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ጭምር ጥያቄ ሲነሳበት ቆይቷል።

ሟቹ ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ፣ በዚህ ረገድ ለሚነሳባቸው ሙግት፣ ዓለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅት አይ-ኤም-ኤፍን በምስክርነት ሲጠሩ ቆይተዋል። ሟቹ ጠ/ሚ የፓርላማ አባላቱን ግንዛቤ ጭምር ለመፈታተን፣ መረጃ መሰብሰብ ይማይችለውን አካል ለምስክርነት ሲጠሩ፣ ይህ እውነት መስሏቸው ያመኑና ያስተጋቡ፣ በየዋህነትም ይህንኑ የሚጠቅሱ መኖራቸው እርግጥ ነው። የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገትን በተመለከተ፣ በሁሉም ዘርፍ መረጃ መሰብሰብ የሚችለው፣ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ብቻ በመሆኑ፣ የሚሰጠው ምስክርነትም የመንግስትን መረጃ መሰረት ያደረገ ብቻ ይሆናል።

መንግስት ይፋ በሚያደርገው የተጋነነ አሃዝ፣ ይህንንም ወስዶ መንግስት አደገ ባለ መጠን አደገ ብሎ መመስከር አማራጭ የሌለው መሆኑን ከስርዓቱ ጋር በአድርባይነት የተጣበቁ ኢኮኖሚስቶችም የማይክዱት ሲሆን፣ ልዩነቱ ወይንም የእነርሱ መከራከሪያ የሚሰበሰበው መረጃ ትክክል ነው የሚል ነው።።ስርዓቱን በሚቃወሙ ኢኮኖሚስቶች፣ እንዲሁም በሌሎች ገለልተኞች ጭምር በኢትዮጵያውያን ህይወትና የኢኮኖሚ ዕድገት አሃዝ ላይ የሚታየው ልዩነት በመረጃዎቹ ላይ ጥያቄ ሲያስነሳ ቆይቷል።ግብርናው በከፍተኛ አሃዝ ስለማደጉ እየተገለጸም፣ እነዚያ በከፍትኛ መጠን አደጉ ያተባሉት ምርቶች በገበያ ላይ፣ የሁለት መቶ-በመቶ እና የሶስት መቶ-በመቶ ጭማሪ፣ አንዳንዴም ከዚያም በላይ መሄዳቸው፣ ከተጨባጩ የኢትዮጵያውያን ኑሮ ባሻገር፣ ለጥርጣሬያቸው ማጠናከሪያ፣ ለአሃዙ ሃሰትነት መደምደሚያም ሲያደርጉት ቆይተዋል።

የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራምን ጨምሮ፣ በዓለም ላይ አሉ የሚባሉ የጥናት ውጤቶች በሙሉ በአንድ ድምጽ የተስማሙበትንና ኢትዮጵያን በድህነት ያለም ግርጌ ያስቀመጡበትን እውነታ፣ ሕዝቡ በኑሮው የሚዳስሰውን ሃቅ፥ ስልጣን ላይ ያሉት ወገኖች በፕሮፓጋንዳ ሊሸፉት፣ በድግስና በጉርሻ ሊያረክሱት ከመንደር እናቶች እስከ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ባለቤቶች ገንዘብ መርጨት መቀጠላቸው በድርጊት እየተገለጸ መጥቷል። ዘመን ያመጣቸው፣ ግሎባላይዜሽን በፍጥነት ወደ እያንዳንዱ ጎጆና ኪስ ያስፋፋቸው ሞባይል ቴሌፎንና ኢንተርኔት፣ እንዲሁም የኢንተርኔት ቱርፋቶች የሆኑ የመረጃ፣ የግንኙነትና የእውቀት ምንጭ የሆኑት ቴክኖሎጂዎች፣ በትናንሽ ሃገራት፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት በማያውቃቸው ጥገኛ ግዛቶች ውስጥ ጭምር ለህጻናት መጫወቻነት በተረፉበት፣ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ለኢትዮጵያውያን ዛሬም ብርቅ ሆነው ቀጥለዋል።

ከመጠን ባለፈ ፍርሃትና የስልጣን ስስት ውስጥ ያሉት የሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ መሪዎች፣ ከዓለም ወደኋላ የንተቱን፣ አንድም በዕውቀት ማነስ፣ በሌላም በኩል፣ የዓላማ ግጭትና የቴክኖሎጂ ፎቢያ ባስከተለባቸው ቀውስ በመሆኑ፣ እነርሱ እስካሉ ድረስ ወደ ዓለምና ወደ ቴክኖሎጂ የምናደርገው ጉዞ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ተረት-ተረት ሆኖ ይቀጥላል። ጎረቤቶቻችን ኬንያና ሱዳን ሳይቀሩ ከሕዝቦቻቸው ከሩብና ግማሽ በላይ የሚሆነው፣ የኢንተርኔት ተጠቃሚ

በሆነበት በዚህ ዘመን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዓለም ጠርዝ ላይ ጥለው፣ በሁለት በመቶ (2%) ላይ ገድበው ከመንግስት-አልባዋ ሶማልያ ጋር ያስተካከሉን የሕወሃት ሰዎች፣ የአፍሪካ ሕዝብ በአማካይ በቤተሰብ ደረጃ፣ ዘጠኝ ነጥብ አንድ በመቶ (9.1%) ኮምፒውተር እየተጠቀመ ባለበት በዚህ ዘመን፣ ኢትዮጵያ በኮምፕዩተር ተጠቃሚነትም ሶስት መቶ እንኳን ባልደረሰችበትና ሁለት ነጥብ ስምንት (2.8) ላይ በተገታችበት፣ በአንጻራዊ መልኩ ኮምፒዩተር በሌለበት “የኮምፒዩተር ወንጀል ለመከላከል” በሚል ስልጣኔን ለማፈንና ትውልድን ከድንቁርና ጋር ለማቆራኘት፣ አደንቁረውም በድንቁርናና በዘረኝነት እየገዙ መቀጠሉን ግባቸው አድርገው ተገኝተዋል። የኢኮኖሚ ዕድገቱን በተመለከተ ለሚነሳው ውዝግብ፣ የችግሩ ምንጭ ሆኖ የሚጠቀሰው፣ በመንግስት የሚሰበሰበው መረጃ፣ ባንድ በኩል የተሳሳተ፣ በሌላ በኩል የተጋነነ በሙሆኑ ሲሆን፣ ይህም ስልጣን የያዙት ወገኖች ሆን ብለው - አቅደው ከሚፈጥሩት ማዛባት ባሻገር፣ የመረጃ አሰባሰቡ ላይ ያለው ውጥረት እንደተጨማሪ ችግር ይጠቀሳል።

በአገልግሎት ዘርፍ ከሚታየው ዕድገት ውጭ በግብርናውም ሆነ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያለው እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑ፣ በሃገሪቱ ውስጥ የሚታየው ማኅበራዊ ቀውስ የሚያረጋግጠው ቢሆንም፣ ዳታውን ወይም መረጃውን በሌላ መንገድ መሰብሰብ የሚቻልበት ሁኔታ ባለመኖሩ፣ ልዩነቱን በተጨባጭ ለማሳየት ሳይቻል ቀርቷል። ሆኖም ውሸትን እንደነውር የማያዩት፣ ለማጣራት አስቸጋሪ የሆነውን ጉዳይ እንደፈለጋቸው ሲለጥጡና አስር ዓመት ሙሉ አስራ አንድ በመቶ (11%) አደግን ሲሉ የዘለቁት ወገኖች፣ በቀላሉ የማይጣራውን ሲያደርጉት እንደዘለቁት ሁሉ፣ በተጨበጭ የሚጋለጡባቸውን የነውር ድርጊቶችን ሲሰሩም ቆይተዋል። በዚህ በግንቦት ወር ባንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በተከታታይ እጅ-ከፍንጅ የተያዙበት ድርጊት፣ “ሕወሃት/ኢሕአዴግን ማመን ቀብሮ ነው” የሚለውን ብሂል ይበልጥ እንድናስታውስ ያደርገናል። የአፋር ሕዝብ ቁጥር ከአንድ ነጥብ አራት (1.4) ሚሊዮን ባልበለጠበት፣ ከሕዝቡ ቁጥር የሚበልጡ ሕፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መግባታቸውን ዋልታ ኢንፎርሜሽን የተባለው የሕወሃት ሚዲያ የዘገበው ከዓመታት በፊት ሲሆን፣ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ፣ እንዲህ ያሉ የሚያሳፍሩና የሚያስገምቱ ዘገባዎችን በተወሰኑ ጊዜያት ማየት እንግዳ ነገር አልነበረም።

በዚህ በያዝነው የግንቦት ወር፣ ለግንቦት 20 ፣ ሃያ-አምስተኛ ዓመት በዓል ድምቀት ሲባል የተለቀቁት የሃሰት ዘገባዎች ግን ተከታታይ ሲሆኑ፣ በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን የተጋለጡትም ወዲያውኑ ነበረ።በደቡብ ኢትዮጵያ፣ አርባ ምንጭ፣ ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ አካባቢ ከታጠቁ ኃይሎች ጋር ማለትም ከአርበኞች ግንቦት ሰባት ጋር የተደረገውን ግጭት፣ ከኢሳት በሰማን ማግስት፣ ማረጋገጫ የሰጠው የሕወሐት መንግስት፣ ታጣቂዎቹ ከኤርትራ በአውሮፕላን ኡጋንዳ ተጉዘው፣ በመኪና ኬንያን አቋርጠው፣ ኢትዮጵያ ደረሱ ይላል። ጥቃት ሳይሰነዝሩም በቁጥጥር ስር አዋልኳቸው ሲልም ገለፀ። የተማረኩ የጦር ማሳሪያዎች በማለት በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና በሌሎችም መንግስታዊ ሚዲያዎቹ ያቀረበው መሳሪያም፣ ከአስር ዓመታት በፊት ኢራቅ ወስጥ የተማረከ መሆኑም ወዲያው ተጋለጠ። መጋለጡን ተከትሎም የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ያሳሳተኝ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ነው ሲል ይቅርታ ጠየቀ።

ሪፖርትም ሆነ ፎቶ የሚቀርበው ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት መስሪያ ቤት በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ፣ ዜና እገልግሎትን መወንጀሉ፣ የመንግስት ዕቅድ ሳይሆን፣ የጋዜጠኞች ስህተት እንዲመስል የተቀነባበረ መሆኑ ግልጽ ነው። ልቦለድ ክሶችን በማቀነባበር ንጹሃንን ወደ ወህኒ ሲነዳ ጠያቂ የሌለው የደህንነቱ መስሪያ ቤት፣ ልቦለድ ፎቶ የለጠፈው፣ ዘመኑ እንደደርሱ የቆመ ስለመሰለው ብቻ ነው። ሌላው ለግንቦት ሃያ አምስተኛ በዓል ድምቀት ሲባል የተቀነባበረው የሃሰት ሪፖርትና ፎቶ፣ ከቻይናና ከቱርክ ባንክ በብድር በተገኘ ገንዘብ፣ ከአዋሽ እስከ መቀሌ የሚሰራውን የባቡር ፕሮጀክትን በተመለከተ የተሰራጨው ፎቶግራፍ ነው። በካሊፎርንያ ግዛት የሚገኘውንና ከሶስት ዓመታት በፊት ተገንብቶ ያለቀውን ዴቭልስ ስላይድ የተባለውን ጥንድ ዋሻ፣ የአዋሽ-ወልዲያ ሃራ ገበያ ዋሻ ባማለት የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት አሰራጨው።

ይህም በማኅበራዊ ሚዲያ አክቲቪስቶች ወዲያውኑ ሲደረስበት፣ የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤትም ይቅርታ ጠየቀ። የካሊፎርንያው ዴቭልስ ጥንድ ዋሻዎች፣ እያንዳንዳቸው ርዝመታቸው ከአንድ ኪሎ ሜትር በላይ የሆኑ፣ የመኪና መንገዶች ሲሆኑ፣ የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት መዋሸቱ ሳያንስ፣ የባቡርና የመኪና መንገድን ሳያጣራ ለቅጥፈት መነሳቱ ከማሳፈርም በላይ ነው። ሰዎቹ ለግንቦት ሃያ በዓል ድምቀት ሃሰተኛ ሪፖርቱን በመቀጠላቸው፣ የዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ዓመታዊ ጉባዔ በቀጠዩ ዓመት በኢትዮጵያ ይካሄዳል ሲሉ፣ የሕወሃት ንብረት በሆነው በራድዮ ፋና በኩል ዘገቡ። ቀጣዩ የፊፋ ጉባዔ በማሌዥያ - ኩአላላምፑር መሆኑ በአክቲቭስቶቹ ሲደረስበት፣ ራድዮ ፋናም ይቅርታ ጠየቀና የፊፋ ሳይሆን፣ የአፍሪካው-ካፍ ነው ሲል ማረሚያም አወጣ። የፊፋን ጉባዔ ማዘጋጀት ትልቅነትንና ስኬትን ያሳያል የሚል መንጠራራት መሆኑ ግልጽ ነው።

እንዲህ ሜዳ ላይ የተበተነንና በኢንተርኔት ባህር ውስጥ የተከማቸን እውነት በአንድ ወር ሦስት ጊዜ ሲሸፍጡ የተያዙ ወገኖች እያንዳንዱ አርሶ አደር ያመረተውን ምርት፣ በቀበሌና በወረዳ፣ በዞንና በክልል እንዲሁም በሃገር-አቀፍ ደረጃ ሲያመጡትና ሲያጣምሩት፣ ምን ያህል ሊዛባና ሊያጋንኑት እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም። በሃገሪቱ እነርሱ ሲመጡ ይመረት ነበር ያሉትን 73 ሚሊዮን ኩንታል፣ ወደ 278 ሚሊዮን አድርሰናል፣ በምግብ ራሳችንን ችለናል እያሉ ገና ድርቁ ሳይመጣ እንኳን ስንዴ ሲገዙ መኖራቸው የአደባባይ እውነት ነውና የሚደበቁበት ቀዳዳ የላቸውም። ጤፍን ጨምሮ

የሰብል ምርት በከፍተኛ ደረጃ ስለማደጉ እየተናገሩ፣ ደርግ ሲወድቅ፣ 105 ብር የነበረው የአንድ ኩንታል ማኛ ጤፍ ዋጋ፣ ዛሬ ወደ 1500 ብር ስለተጠጋበት ምክንያት ማስረዳት አልተቻላቸውም። በመጀመሪያዎቹ አስር የስልጣን ዘመናቸው፣ እስከ 1992 ዓ/ም ፣ የጤፍን ዋጋ ንረት በአንጻራዊ ጠብቀው በ 285 ብር ላይ አቆይተዋል። በምርጫ 1997 ም አንድ ኩንታል ጤፍ 310 ብር ነበር። ባለፉት አስር ዓመታት ሁሉ ነገር ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጣ ያደረጉት፣ ከመጠን በላይ ገንዘብ በማተም፣ እንዲሁም ከመጠን በላይ ብድር በማስገባትና እነርሱም በከፍተኛ ደረጃ በዘረፉ ውስጥ በመሰማራታቸውም ጭምር ነው።

አዎን! የሕወሃት/ኢሕአዴግን 25 ኛ ዓመት በዓል ለማክበር ሃሰተኛ ሪፖርቶቹ መጠናቸው የጨመረው፣ እንዲሁም ከፍተኛ ገንዘብ በማፍሰስም ድግሱ የበረታው፣ የብር እዩ-በልዩ በዓል ስለሆነላቸው ሳይሆን፣ ዓመቱን ሙሉ ዘንግተውት ድንገት መራወጥን ያበዙት፣ የውስጣቸውን ቀውስ ለመሸፈን ያግዛል በሚል ስሌት ጭምር ሲሆን፣ ሕወሃት እንደ ቡድን 26 ኛ ዓመቱን የስልጣን ጉዞ በውስጣዊና ውጭያዊ ቀውስ ተሰንጎ የሚቀጥልበት በመሆኑ፣ መጪው ጊዜ ብዙ የምናይበት ሲሆን፣ በማናቸውም መንገድ ቢሆን፣ ጨለማው እየተገፈፈ የሕወሃት አገዛዝ እየረገፈ መሄዱ ግን ምኞት ብቻ ሳይሆን የሚዳሰስ እውነት ነው።

እርግጥ ነው ሕወሃቶች ትንፋሽ ለመሰብሰብ እየተራወጡ መገኘታቸው ግልጽ ነው። የተንሻፈፈውን አቅንተን፣ የጎበጠውን አቃንተን፣ የተዳፈነውን የፖለቲካ ምኅዳር አስፍተን እንሂድ የሚሉት ግባቸው እንደ ቃላቸው አለመሆኑም ግልጽ ነው። ከሱዳን አብዬ ግዛት የሰላም አስከባሪ አዛዥነታቸው የተነሱት የሕወሃቱ ሌ/ጄኔራል ዮሐንስ ገ/መስቀልም በጄኔራል ሳሞራ ወንበር ላይ እያንዣበቡ መሆናቸው፣ እንዲሁም ከደህንነት ኃላፊው ጌታቸው አሰፋ ጋር ቅርበት መፍጠራቸው እየተሰማ ሲሆን፣ አርከበ ዕቁባይም በዚህ ዙሪያ እያየናቸው እንገኛለን።

ጡረተኞቹ ጀኔራሎች እነ አበበ ተ/ኃይማኖትም ከዚህ ሂደት ውጭ አይደሉም። ሰሞኑን ከላይቤሪያ ዋሽንግተን የገቡት አቶ ስዬ አብርሃም በሂደቱ ስላላቸው ሚና የታወቀ ነገር ባይኖርም፣ ሕወሃትን መጠገን እንጂ ስር-ነቀል ለውጥ አያስፈልግም የሚለው አቶ ስዬን ጨምሮ ከመድረኩ የተገለሉት የሕወሃት ሰዎች ሁሉ ያጋራ አቋም መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ማለት በአጭርና ግልጽ ቋንቋ ብዙ ስለታገልንና ብዙ ስለሞተብን የበላይ ሆነን መቀጠል ይገባናል ማለት ነው።የማንም የበላይነት የሌለበት፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እኩል የሆኑበት ስርዓት እንዲከተል ደግሞ፣ ሕወሃት መታደስ ሳይሆን፣ መፍረስ ይኖርበታል። አዎን! 25 ኛ ዓመት በዓላቸው የቁም ተስካራቸው እንዲሆን፣ ከምኞት ባሻገር የየአቅማችንን እንወርውር፤ የነጻነት ኃይሎችን እንደግፍ፤ በጎንዮሽ ልፊያ የሚጠፋውን ጉልበትም እንሰብስበው።

**ገ/ፃዲቅ አበራ**